# የቤት ኪራይ ክፍያ አልፎቦታል?



አከራዮት የቤት ኪራይ በማዘግየቶ ምክንያት ሊያስፈራራዎት እየሞከረ ከሆነ **ለዚህም አማራጭ አሎት።** ከቤቱ ተገደው መውጣት የማይፈልጉ ከሆነ የመቆያ ትእዛዝ ወይም የማስለቀቂያ ትእዛዝ ተብለው ከሚጠሩት ውስጥ ሁለት ዋና አማራጮች ይኖራሉ። እነርሱም፡

“**ከፍለው ይቆዩ**” ወይም “**ተስማምተው ይልቀቁ**”

| | የመቆያ ትእዛዝ | ከፍለው ይቆዩ | በስምምነት መልቀቅ |
|---|---|---|---|
| **በተከራየሁት ቤት መቆየት እችላለሁ?** | ምናልባት አይችሉም | አዎ | አይ |
| **ማስጠንቀቂያ በግል ማኅደሬ ላይ ይኖራል?** | አዎ | አይ | አይ |
| **ወደ ፍርድ ቤት መመለስ ይኖርብኛል?** | ምናልባት አይኖርብዎትም | ምናልባት ይኖርብዎታል | ምናልባት ይኖርብዎታል |
| **ለመልቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይኖረኛል?** | 10 ቀናት | የኪራይ ውል መጠናቀቂያ ድረስ | እስከተስማሙበት ቀን ድረስ |
| **መቼ መክፈል ይጠበቅብኛል?** | ቤቱን ከለቀቁ በኋላ | በተስማሙበት ቀን | ቤቱን ከለቀቁ በኋላ |

**NONPAYMENT FLYER**

## ከአከራዮት ጠበቃ ጋር ስምምነት ላይ መድረስ አይጠበቅቦትም።

እምቢ የማለትና **የፍርድ ቤት ቀጠሮ** የመጠየቅ መብት አልዎት። ከፍርድ ቤቱ ቀጠሮ በፊት ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለጎትም ዳኛውን **ማራዘሚያ** መጠየቅ ይችላሉ። ምናልባት የቤት ኪራይ ክፍያዎን ስላዘገዩ፣ ዳኛው በቤቱ ውስጥ መቆየት አይችሉም ብሎ ሊወስንቦት ይችላል።

**ነገር ግን ቤቱን መልቀቅ ቢኖርቦትም እንኳን፣ የሚከፍሉትን ገንዘብ መጠን ለማስተካከል ወይም ቤቱን ለመልቀቅ ተጨማሪ ጊዜ ለማግኘት የፍርድ ቤት ቀጠሮውን ሊጠቀሙበት ይችላሉ።** ዳኛው እሺ ብሎ መስማማት ላይጠበቅበት ይችላል።ነገር ግን እርስዎ የመሞከር መብት አልዎት። በፍርድ ቤት ክርክር ቢሸነፉ እንኳን ለመልቀቅ **አስር ቀን** ይኖርዎታል።

## ክፍያዎን በመፈጸም በቤቱ ውስጥ መኖር ለ“መቀጠል” ወይም ቤቱን ለመልቀቅ ይጠይቁ ከዚያም ጉዳዩን ሲያጠናቅቁ “ፋይሎን ያዘጉ ”

ይህ ማለት ተመልሰው በመምጣት ክፍያዎትን በወቅቱ እየከፈሉ መሆኑን ወይም እለቃለሁ ባሉበት ጊዜ የለቀቁ መሆኑን ለዳኛው መሳየት የሚችሉበት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ይኖርዎታል ማለት ነው። የሚጠበቅብዎትን በሙሉ ከፈጸሙ ወይም ቤቱን ከለቀቁ፣ ቀርቦብዎት የነበረው የማስለቀቂያ ክስ ይሰረዛል ወይም “መዝገቡ ይዘጋል”።

## አከራዮት አለቦት በሚለው እዳ ላይ ካልተስማሙ ተስማምተው እንዳይፈርሙ።

የፍርድ ቤት ቀጠሮ ይጠይቁና ለዳኛው ቁጥሩ ለምን ስህተት እንደሆነ ያስረዱ። በክርክር ቢሸነፉ እንኳን አሁንም ለመልቀቅ አስር ቀን ይኖርዎታል።

እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክርን አይመሰርትም፤ ለመመስረት የታሰበም አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎት ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድ ቢሮ በ1-800-238-1443 ወይም የናሽቪል የሂስፓኒክ ባር ማህበርን በ1-615-701-7957 ይደውሉ።

በ5/23 ተሻሽሏል።